# ሞት ሳይሆን ሕይወት በአባይ ላይ!!

**ታከለ ቢራራ** 08/20/13

የዚህ ጽሁፍ መነሻ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን በተለያየ አቅጣጫ የሰጡትን አስተያየትና ትንተናን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታና የአባይ ውሀ ጉዳይ ዛሬም የመገናኛ ብዙሃን የሞቀ አጀንዳ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በተለይ አልጀዚራ በአባይ ጉዳይ ላይ ተልእኮ ስላለው በቀጥታም ሆነ በአግድም ሳያነሳው አያልፍም፡፡ ‹‹ሞት በአባይ ላይ›› በሚል ላቀረበው መሰሪ ዘገባ ‹‹ሕይወት በአባይ ላይ›› የሚለውን ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው፡

ኢትዮጵያ እጅግ ቀደምት ከተባሉ ጥንታዊ ስልጣኔ ከነበራቸው አገራት አንዷ የነበረች ቢሆንም በድህነትና በጦርነት በድርቅና በረሀብ ውስጥ ለዘመናት ለመኖር ተገዳ ነበር፡፡ ይህንን አስከፊና አዋራጅ ታሪክ ለመለወጥ እንዲቻል ከተወጠኑትና ከተጀመሩት ሰፊ የልማትና የእድገት ፕሮጀክቶች አንዱ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ በመገንባት የተጀመረው ታላቅ ብሔራዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ የግንባታው ሂደት በልዩ ብሔራዊ ትኩረት ቀን ከሌሊት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያና ሕዝቧ የጀመሩትን ይህን ታላቅ ከድህነት የመውጣት እርምጃ የሚገታው ምንም ነገር አይኖርም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከመነሻው እነማን ለምን እንደተቃወሙትና እየተቃወሙት እንዳሉ በግልጽ ይታወቃል፡፡ የአባይን ውሀ የተፈጥሮ አቅጣጫ ማስቀየራችን ይፋ ሲሆን የግብጽ አንዳንድ መሪዎችና ፖለቲከኞች ተገቢ ያልሆነ የጠባ አጫሪነት መልእክቶችን ሲያስተላልፉና ሲያሰራጩ ቆይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም ሰለማዊ ውይይትና ድርድር ዲፕሎማሲ ብቻ እንደሚበጅ እየገለጸች ትገኛለች፡፡

የአባይ ውሀ የተፈጥሮ ባለቤት ማነው ለሚለው ጥያቄ በማያሻማ ሁኔታ 85 ፐርሰንት የሚሆነውን ውሀ የምታመነጨው ኢትዮጵያ መሆኗ አነጋጋሪም፤ አከራካሪም፤ አይደለም፡፡ ኢትየጵያ ይህን የተፈጥሮ ስጦታዋን ብቻዬን ልጠቀምበት አላለችም፡፡ ሱዳንና ግብጽ በቅኝ ገገርዋ እንግሊዝ በ1929 እና በግብጽና ሱዳን በ1959 (እ.ኤ.አ) የተደረጉትን የአባይ ውሀ የኮታ ድልድልና አጠቃቀም መነሻ በማድረግም አባይ ጭርሱንም የተፈጥሮና ታሪካዊ ስጦታችን ነው የሚል በተለይም በግብጽ በኩል የግለኝነት አስተሳሰብ ሲንጸባረቅ ቆይቷዋል።

በነዚህ ስምምነቶች መሰረትም የአባይ ውሀ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉም የላይኞቹ ተፋሰስ ሃገራት በአባይ ውሀ ላይ ለሚያደርጉት ማንኛውም ፕሮጀክት ለግብጽ ማሳወቅ አለባቸው የሚል የቅኝ ግዛት ውል ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ያለፉት የግብጽ መንግስታት የአባይን ውሀ ከመነሻው ለመቆጣጠር ከነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎትና ስሜት በመነሳት ኢትዮጵያን በጦርነት ለመውጋት ዘምተው በተደጋጋሚ ተሸንፈዋል፡፡ የጥንቱን ትተን በ19ኛው

ክ,ዘመን የግብጽ መሪ የነበሩት ኮ/ጀማል አብደል ናስር ነበሩ በኤርትራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመውን የጀብሀ እስላማዊ ፓርቲ እንዲመሰረት ያደረጉት፡፡

ኤርትራ አረባዊና እስላማዊ እንጂ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም በሚል እነ ኦስማን ሳላህ ሳቤንና አዋቴ እድሪስን ግብጽ በገንዘብና በወታደራዊ ስልጠና በመርዳት ኤርትራ ተመልሰው አባላቶቻቸውን እንዲያበራክቱና ውጊያ እንዲከፍቱ በዚህም የነበረውን የኢትዮጵያን መንግስት ውጥረት ውስጥ እንዲከቱ ይህ ቀረሽ የማይባል ትግል አድርገዋል፡፡

እነዚሁ የጀብሀ እስላማዊ ታጣቂዎች በግብጽና በሱዳን ጦር ሰፈር አግኝተውም ነበር፡፡ ተገቢ ወታደራዊና የመረጃ ስልጠና እንዲወስዱ፤ የሬድዮ ጣቢያ እንዲኖራቸውና በአረቡ ዓለምም ሰፊ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ ከጀብሀ ተገንጥሎ የወጣው ሻዕቢያ በወቅቱ ክርስቲያናዊ ክንፍ የነበረ ሲሆን የተቋቋመበትም ምክንያት በስተኋላ የተከሰተው ዓይነት መገንጠል እንዲመጣ ሳይሆን አጼ ኃይለ ሥላሴ ከስልጣን እስከወረዱበት  ጊዜ ድረስ የዛሬው የሻዕቢያ መሪ በልዑል ራስ አስራተ ካሳ የወቅቱ የኤርትራ ዋና አስተዳዳሪ አማካኝነት ውስጣዊ ግንኙነት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ነበረው፡፡

ይህንን እጅግ ከፍተኛ ሀገራዊ የደህንነት ምስጢር ያላገኘውና ያልተረዳው ወደ ስልጣን የመጣው ደርግ በኤርትራ ያለውን የአማጽያን እንቅስቃሴ በጅምላ በአረብ የዘይት ሀብት የተገዙ የፔትሮ ዶላር ቅጥረኞች ኤርትራን ሊያስገነጥሉ ነው በሚል የመጨረሻው ወደሆነ የጦርነት እርምጃ ተሻገረ፡፡ ሻዕቢያም ጃብሀን በመምታት ወደ ከፋ ጦርነት ገባ፡፡  ግብጾች ለሻዕቢያ ማንኛውንም ድጋፍ በማድረግ እንደተለመደው ኢትዮጵያን ከጀርባ መውጋቱን ለረዥም ግዜ ገፉበት፡፡ ይህ የገብጽ ተግባር ለኤርትራ ህዝብ በእውነት ከመቆርቆር ሳሆን የኢትዮጵያን  ሰላምና ደህንነት በማወክ ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የቆየ ጥቅሙን ለማስከበር ከሚል መሆኑን ብዙዎች ይገልጻሉ፡፡

ግብጽ ጀብሀን ስታቋቁም የነበራት እምነት በኋላም በሻዕቢያ ኤርትራን ሙሉ በሙሉ ነጻ በማውጣት ከላይ ሆነን የአባይን ውሀ ምንጭ ለመቆጣጠር ቀላልና አመቺ ይሆንልናል የሚል ነበር፡፡ ኤርትራ ራሷን ችላ ብትወጣም የግብጽ ሙሉ እርዳታና ምክር ድጋፍና እገዛ አልተለያትም፡፡

በኤርትራ በኩል የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ሀይሎች ወታደራዊ ስልጠና ማሰልጠን ማስታጠቅና ሀይል ማደራጀት፤ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሰርገው እየገቡ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር የማድረጉ የመጀመሪያው ሴራና እቅድ የግብፅ ሲሆን፣ አሁንም ሻዕቢያ በተላላኪነት ይሄንኑ ተግባር እያስፈጸመ ይገኛል፡፡ ተቃዋሚዎች በኤርትራም በግብጽም ጽ/ቤት የሬዲዮ ስርጭት ፕሮግራምም አላቸው፡፡ ይህ በገንዘብ የሚደገፈውና የሚረዳው በዋነኛነት በግብጽ መንግስት ነው፡፡ ዓላማውም በኢትዮጵያ ሰላም ያለውና የተረጋጋ መንግስት እንዳይኖር፤ የአባይ ወንዝ

እንዳይገድብ ሁሌም በትርምስና በውጥረት ውስጥ እንድትኖር ለማድረግ የተጠነሰሰ ሴራ መሆኑን ትላንትም የነበሩት ዛሬም ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

የዚያድ ባሬ መንግስት በምስራቅ ኢትዮጵያ ወረራ ሲፈጽምና ሲወጋን ከጀርባ ሙሉ እገዛ ያደርጉ የነበሩት የቀድሞዎቹ የግብጽ መንግስታት ነበሩ፡፡ ሶማሊያ ከፈራረሰችም በኋላ ሶማሊያ ውስጥ ለተፈጠሩት የተለያዩ የጦር አበጋዞችና አንጃዎች የገንዘብና የመሳሪያ የወታደራዊ ስልጠና ድጋፍና ማማከር የሚሰጡት ግብጽና የስለላ ተቋማ ነበር፡፡በሁዋላም ሻእቢያ ተጨምራል፡፡

ኤርትራ ራሷን ችላ እንደመንግስት ከቆመችበት ግዜ ጀምሮ የግብጽን ውክልና በመውሰድና ዓላማዋን በማራመድ፣ ኢትዮጵያ ጠንካራ ሀገርና መንግስት እንዳትሆን ከድህነትና ከተረጂነት እንዳትወጣ ስለልማትም እንዳታስብ፣ ሁሌም በአራቱም ማዕዘናት በጦርነት የተወጠረች፣አቅሟ የተበታተነና የደከመ ለማድረግ ብዙ ደክመዋል፡፡

ኢትዮጵያን የሚቃወም ማንኛውንም የፖለቲካ ሀይል በገንዘብም በወታደራዊ ስልጠናም በመረጃም በምክርም አገልግሎት ይረዳሉ፣ያግዛሉ፡፡ አቅማቸው በፈቀደና በቻሉት መጠን አንዳንድ ተቃዋሚዎችን በማደራጀትና በማስታጠቅ ከጀርባ ሆነው ኢትዮጵያን ለማተራመስ ያላቸውን እቅድም በሚስጥራዊ ስብሰባቸው ይፋ ያደረጉበት ሚስጥርም ከቢሯቸው ሾልኮ ሴራቸው የተጋለጠበት ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ማስረጃ ነው፡፡

ከተረጂነት የወጣች  የበለጸገችና ጠንካራ ኢትዮጵያን ማየት አይፈልጉም፡፡ በዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የሚመራው ግንቦት ሰባት ከኤርትራም ከግብጽም መሪዎች ጋር እጅና ጓንት ሁኖ በመስራት በታላቅ ሀገራዊና ሕዝባዊ ክህደት ተሰልፎ ይገኛል፡፡ የአባይን ግድብ መገንባት ጭርሱንም ከማይፈቅዱና አሁንም ደግሞ ግድቡን እንመታለን እያሉ ከሚያቅራሩ ጸረ-ኢትዮጵያ ሀይሎች ጋር መሰለፍ ‹‹መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል›› የሚባለውን ሀገራዊ ተረት በግንቦት ሰባት በመሳሰሉት ላይ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡ ‹‹የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መፈክር በመታጀብ ኢሕአዴግን በጠላትነት ስለፈረጁ የሚመራትን ሀገርና 85 ሚሊዮን ሕዝብ የልማትና የእድገት ተነሳሽነቱን ከድህነት ለመውጣትና ታሪክን ለመቀየር የሚያደርገውን ትንቅንቅ በማውገዝ ከጠላት ጋር መሰለፍ በታሪክና በትውልድ እጅግ የከፋውን ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡ እነግንቦት ሰባት፣መድረክና አንድነት፣ ሰማያዊ ፓርቲና ሌሎችም ከአክራሪው እስላማዊ ሀይል ጋር በመሆን አክራሪነት በኢትዮጵያ የለም፣አልተከሰተም በማለት ድጋፍ ፍለጋ እየባዘኑ ይገኛሉ፡፡

በመጅሊሱ አመራርና በአወሊያ ት/ቤት ዙሪያ ተከስቶ የነበረውን አለመግባባትና ውዝግብ ለመፍታትም ሁለቱንም ወገኖች በማደራደር ምላሽ ተሰጥቶ እንደነበር ይታወሳል። በዚህም መሰረት የአመራር ምርጫም ተካሂዷል፡፡ ይህን ያልተቀበሉ ወገኖች ሙስሊሙን ብቻ ሳይሆን

መላውንም ሕብረተሰብ ወደሁከትና ብጥብጥና ትርምስ ውስጥ የሚያስገባ ተግባር ላይ በመሰማራታቸው፣ ሰላም ጸጥታና ደህንነት የማስከበር ብሔራዊ ሃላፊነት ያለበት መንግስት ግለሰቦቹ ሕግፊት እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡

ይህንን መንግስታዊ ሃላፊነትና ተግባር እያወቁ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በሃይማኖት ጉዳዩች ጣልቃ ገብቷል፣ የሙስሊሙን የእምነት ነጻነት ረግጧል፣ ደፍሯል፣ አስሯል፣ በሚል አንዳንድ የአረቡ ዓለም ሚዲያ በተለይም የግብጽ ሚዲያዎች ሁኔታውን በማራገብ፣ በኢትዮጵያ የሀይማኖት ነጻነት አይከበርም በሚል ዓለም አቀፍ ዘመቻ ለመክፈት ተንቀሳቅሰዋል፡፡

በአሜሪካን የተቋቋመው ሂጅራ ፋውንዴሽንም ከግብጽ መንግስት ጋር በተቀናጀ አጀንዳ እንደሚንቀሳቀስ፣ ከግንቦት ሰባት ጋር አብሮ እንደሚሰራ በቅርቡም በአዲስ አበባ የተቃውሞ ሰልፍ ከጠራው ሰማያዊ ፓርቲና አመራሮች ጋር በመጣመር አብዛኛው ሙስሊም ለተቃውሞ እንዲወጣ የውስጥ ለውስጥ ጥሪ በማስተላለፍና በማስተባበር በኢትዮጵያ ውጥረት ለመፍጠር የተጠነሰሰው ሴራ ከጀርባ የውጭ ሀይሎች እጅ እንዳለበት ይታወቃል፡፡

ብሔራዊ ጥቅምን፣ ሀገራዊ ጸጥታና ደህንነትን፣ የጸረ-ኢትዮጵያ ሀይሎችን ጥንታዊና የቆየ ሴራና ውጥን፣ በቅጡ ለይተው የማይረዱ እያወቁም በመተባበር የተሰለፉ በስም ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ፣ በተግባር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚወጉ ተቃዋሚ ነን ባዮች ቀረበም ዘገየ በታሪክም በሕዝብም ተጠያቂ ናቸው፡፡ የቆየው የግብጻውያን ሴራ በአዲስ መልክ በቤተመንግስቱ ባደረጉት ውይይት በቀጥታ በቴሌቪዥን ለግብጽ ሕዝብም ለዓለምም መተላለፉም ምን ያህል ሴራ ከጥንት እስከ ከአሁን በኢትዮጵያ ላይ ሲውጠነጠን እንደኖረና አሁንስ በመካሄድ ላይ እንዳለ ድፍን ዓለም ተረድቶታል፣ታዝቦአቸዋልም፡፡ በዚሁ ውይይት የተነሳው አንዱ ነጥብ የኢትዮጵያን ተቃዋሚዎች ማገዝና መርዳት የሚለው ነጥብ

የግብጽ ፖለቲከኞች በኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ባደረጉት ውይይት አደገኛ ስለሆነ ሊቆም ይገባዋል የሚለው መደምደሚያ በግብጽ የዲፕሎማሲ ታሪክ የክፍለ ዘመኑ ውርደት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የግብጽ ፖለቲካ አስተዋይነትና ብስለት በጎደላቸው ሰዎች እጅ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በእርግጥ በሳል የሆነ አስተዋይ ተቃዋሚዎችም አልታጡም፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ የአባይ ውሀ ዋነኛ መገኛ የሆነችውን ኢትዮጵያን በፍቅርና በወዳጅነት መያዝ ነው ወይንስ ፋይዳ የሌለው ጦርነት መመኘት? የአባይ ውሀ ብቸኛ ታሪካዊ የባለቤትነት ድርሻ አለን የሚለው የግብጽ ተረት ተረት ከየትነው የመጣው? ማነው ባለቤትስ ያደረጋቸው?የሚሉት ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡

ኢትዮጵያ አንድም ቀን በታሪክ በአባይ ውሀ ሱዳንና ግብጽ እንዳይጠቀሙ ያለችበት ይሄን ለማደናቀፍ የሰራቸውም ስራ የለም፡፡ አሁን እየተሰራ ያለውም የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግብጽም ሆነ ሱዳን ሊያገኙት የሚገባቸውን ድርሻ አይቀንስም፣ ውሀው የሀይል ካመነጨ በኋላ ተመልሶ

የተፈጥሮ ፍሰቱን ይቀጥላል፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ መንግስት በተደጋጋሚና ያለመሰልቸት ለሱዳንም ለግብጽም መንግስት ለሕዝቦቻቸውም ለማስረዳት ጥረት አድርጓል፡፡

የናይል ተፋሰስ ሀገራት በዚህ ግድብ መሰራት ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ እንደማይሆኑ በማመንና በመቀበል ስምምነት ፈርመዋል፡፡ በግልጽነት መርህ የተመሰረተው የሶስትዮሽ ኮሚቴ (ከግብጽ ሱዳንና ኢትዮጵያ ገለልተኛ አካላትንም አካቶ) ያደረገውን ጥናት ከራሱ እይታ አንጻር ይፋ አድርጓል፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራዊ ልማቷን ከማፋጠንና ሕዝቧን ከድህነት ከማውጣት በስተቀር የተለየ የጦርነት አጀንዳ የላትም፡፡ ሰላምን አክባሪና ለሰላምም የምትቆም ሀገር ነች፡፡

የሱዳንም ሆነ የግብጽ ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር የጠበቀ ታሪካዊ ግንኙነትና ትስስር እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ ውጭ የግብጽ መሪዎችም ሆኑ ፖለቲከኞች የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ እያራመዱት ያለው የተሳሳተ የጦረኝነትና የተንኳሽነት ሚና ለግብጽ ሕዝብ አይጠቅምም፡፡ ድርጊታቸውም ታሪካዊ ስህተት ከመሆን ባለፈም፤ ከዚህ ዘመን በሳል ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ጋር የሚጣጣም አይሆንም። ችግሮች አሉ ከተባለ በጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይቶ መፍታት ይቻላል፡፡ ጦርነት መቼውንም ቢሆን መፍትሔ አያመጣም፡፡ የኢትዮጵያ እጆች ለሰላምና ለዲፕሎማሲ ተዘርግተዋል፤በአባይ ወሀ ላይ ሞት አይኖርም፤ ህይወት እንጂ፡፡